# ይቅርታ ምንድነው?

አምናን እማ እንርሳው ፡ የዘንድሮን ብቻ
በደም ሰክረን ነበር ፡ በሥልጣን ኮሪቻ
ከበርን ነገድን ፡ ስንዘራ ጥላቻ
ዛሬ ሁሉም ቀርቶ ፡ ያሳደው ዘመቻ
ይኸው አደረገን ፡ ከደሃው ጋር አቻ ።

ይቅርታ ምንድነው ፡ ለኢትዮጵያ ልጅ
ግራ ቅኝ ሸውዶ ፡ ማወናበድ እንጂ
ሰርቀን ብንከብር ፡ ደም እንኳ ቢፈስም
ሰው አለወንጀሉ ፡ ብናስር ብንከስም
በጎሣ ከፋፍለን ፡ አገርም ብናፈርስም
ጴንጤ ከተሆነ ፡ ሰው አይከሰስም ።

ይቅርታ ምንድነው ፡ አገር አይሆን ዳቦ
የተረሳን ታሪክ ፡ ጎቶት ሰብስቦ
የሰው ቀልብ መግፈፍ ፡ ግራ ቀኝ አዋክቦ
በየሱስ ሥም ጎበዝ ፡ አትነካኩኝ አቦ ።

ከሰላማዊት. አ